ምጥ ማቅ ልደት ትንሣኤ

ተሰጠ ከተወልደ መድኅን ዘብሔረ አግዓዚ

ግንቦት ፳፩ ቀን ፳፻፲፩ ዓ/ም

(መልእክቱን በአስቸኳይ ለሕዝብ እንዲደርስ በትየባው ለተባበሩ ምስጋና እያቀረብን የሞክሼ ፊደላት ግድፈት ወይም ሌላ ቢኖር ከይቅርታ ጋር አንባቢ እያረመ በትእግስት እንዲያነበው እንጠይቃለን።**)**

የሚያነብ ይረዳው፡ የተረዳው ያስረዳ። ይህ መጽሐፍ ሸቀጥ አይደለም። አቅሙ ኖሮት አባዝቶ በነጻ ሊያከፋፍለው የሚሻ ቢኖር ይህ ነጻ ነው ብሎ አትሞበት አባዝቶ በነጻ እንዲያሰራጨው ፍቃድ አለው። የሚያሳትመውም የዚህ መጽሐፍ ባለቤት አይደለም፡ ቃላቱም መልእክቶቹም የእሱ አይደሉም፤ እኔ መጭውን ለሕዝብ እንድገልጥ እንዲሁ እሱ ደግሞ እንዲያስተላልፍ ትእዛዝ ፈጻሚ እንጂ።

በዚህ መልእክት የጌታ መንግሥት ይክበርበት። ኢትዮጵያም ትዳንበት።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

ይህ መጽሐፍ ድርሰት አይደለም፡ ምዕራፍ የለውም፡ የትንቢት ማስታወሻ፡ የትንቢት ፍጻሜ እንቢልታ እንጂ የእኔ ትንቢት አይደለም፡ ይዘቱም ቃላቶቹም እንደመጡልኝ ያሰፈርኳቸው እንጂ ቅደም ተከተል የላቸውም። ይህ መጽሐፍ ስለኢትዮጵያ ህልውና ለተላኩ መልእክቶች ሁሉ እናት ነው። የመንገድ ቅያስ ማሳያ ነው። የዛሬዋን ዓለም ገዥ ገላጭ ነው። እንኳንስ ስለኢትዮጵያ ስለሌላውም አባቶች ገልጸዋቸው የነበረ እኔም እንድጽፋቸው የታዘዝኳቸው፡ ዛሬ ላይ ሆኜ ያለፈውን እንደአየሁ ሁሉ መጭውንም በእኔ ጽድቅ ሳይሆን በአባቶች ጽድቅ፡ በጌታ ቸርነት ምክንያት ስለወደፊት በዐይነ ኅሊናየ የተረዳሁትን ነው። ይህንን አንብቦ ያልተረዳ የጋኔኑ አዚም በሽተኛ ነው።

እኔም ይህን እንቢልታ በጽሑፍ እንደማስቀምጥ፤ ለሕዝብም እንደምገልጥ ሳላውቅ በፊት ይህ ጸሊም ገዥ እኔ እንደምገልጠው ያውቀው ነበር። ከልጅነቴ ጀምሮ ሊያስወግደኝ ሞከረ፤ ኤልሻዳይ ግን አልፈቀደለትም። በአንድነቱ በሦስትነቱ ጸንቶ የነበረው ያለው የሚኖረው ኅያል ጌታ ከሞት አፋፍ መለሰኝ፤ ከሕመሞች ከደዌያት ሁሉ ፈወሰኝ፤ ሳልማር አስተማረኝ፤ ታሪክን ሳላነብ ወደኋላ ወስዶ አሳየኝ፤ ታሪክን ከታሪክ አዋቂዎች በላይ አሳወቀኝ፤ እነሱ ታሪክን አንብበው፤ ሲተረክም ሰምተው አወቁ፤ እኔ ግን ታሪክን አየሁት፤ አወቅሁት፤ እነሱ ያላዩትን ግን የተረኩትን እኔ አየሁት አወቅሁት፤ ብዙዎቹንም ገመትኳቸው፡ እንዲሆን

የፈለጉትን ግን ያልሆነውን ሆነ ብለው ስለጻፉ፡ ትውልድንም ስለዋሹ፡ የሃገር አባቶችንም የጌታን ባሮች ሰድበው ስለአሰደቡ የተናቁ ሆኑ።

ለጎያሉ የአብርሃም ጌታ ምን ይሰነዋል? ጻድቅ አይደለሁም፤ ከቅድስናም የራቅሁ ስለሆንሁ የዓለምን መከራዋን አውቀዋለሁ። የፍቅሩ ብዛት ከልቤ ተራራ ላይ እንደ አባይ ወንዝ እየፈሰሰ ቢያስጨንቀኝ እንኪንስ ከአሕዛብና ከኃጥአን ከከበሩትም በላይ ከፍ ያልሁ መሰለኝ። እሱም ፍቅሩን ከልቤ ቋት ቀብሮ ተሰወረኝ፤ እኔም በዓለም ያለውን ኃጢአት በአካልም በመንፈስም በቁጣም በስንፍናም ሠራሁት። በአካል የሰው ነፍስ አላጠፋሁም ግን በመንፈስ የብዙዎችን ሞት ተመኘሁ፤ በሥጋም የዝሙት ነገሮችን ሁሉ ሠራሁ፡ የተመኘ አደረገ እንዲሉ። ከኖ ምን ያላጠፋሁት ያልበደልሁት አለ? ጌታ ሲቀርበኝ አውቀዋለሁና ደስ እሰኛለሁ፤ ከፍ ከፍም እላለሁ፤ ከዛም ዝቅ ሊያደርገኝ ከፍ ብሎ ይሰወራል፤ እንደለመድኩትም ወደጨለመው ጎሊናዬ እመለሳለሁ። እንዲህ እያደረገ ቅዱሱ ኮተኮተኝ። እኔም የዓለም ምስጢር፤ የደጎች የጻድቃን የውድቀት ምስጢር የተገለጠለኝ ታላቁን ያየሁ ታናሽ ሆንሁኝ፡ በሥጋ ዐይኖቼ ያየሁትን ብዙ የሰው ልጆች አላዩም፤ ሳልሞትም ነፍሴ ከሥጋዬ እየተለየች ዓለምን ከላይ ቃኝታለች፡ የነፍስን ነጻነት አይታለች። ዛሬ ይህን ስጽፍ ያዕቆብ የታገለውን ጌታ ለምን ስለፍቅሩ ስታገለው እዚህ እድሜዬ እንደደረስሁኝ

ተገለጠልኝ። የዘመኔ ጥያቄ፤ ስለምን ማወቅ የማይገባኝን፤ ለማወቅ የማልፈልገውንም እንዳውቅ አስጨነቅኸኝ ነበር። ስለምንስ ሳልፈልግ ያልሆንሁትን ሆንኩ፤ የምጠላውንስ ስለምን ሳደርግ ዝም አልኸኝ፤ ለመውደቅ ስንገዳገድና አድነኝ ብዬ ስለምንህ በዝምታህ ስወድቅ አየኸኝ? ስለው ኖርኩ።

አሁን ግን የተመረጡት ወድቀው ሳይ፤ የወደቁበትም ጉድጓድ እኔ ጠልቄበት ከማዉቀው ጥልቅ ርቆ ሳየው ለምን ዝም እንዳለኝ ገባኝ። የጌታ ዝምታ ፍቅር ነው፤ ጥላቻና ርቀት ቢመስልም። የተመረጡትን ስላፈቀራቸው እነሱ ላይ ሌላው ጣቱን እንዳይቀስር የቆመ የመሰለው ሁሉ ከመጋረጃው ጀርባ ወድቋል። ወድቆ በወደቀው የሚጠቋቆም ሁሉ ለከፋው ውድቀት የሚሮጥ ደካማ ነው። ያልወደቀ የለም። የተመረጡት ግን የወደቁት ተጠልፈው ነውና የውድቀታቸው እውቀትም አብሮ ተጠልፎ በደስታ እንዳልወደቁ ቆመው ይሄዳሉ፡ በከፍታቸው ወቅት ጽድቃቸው ሲገለጥ የማይወደው በውድቀታቸው መንገድ ላይ ሌሎች እንዲሰናከሉ የቀደመ ጽድቃቸውን ገለጠው። ጠላፊው ብርያል ኃጢአታቸውን፤ ክስረታቸውን ሲገልጥባቸው አንዳንዶቹ አምላክን ጠልተው ይደበቃሉ፤ ከፊሎቹም እራሳቸውን ያጠፋሉ፤ የተቀሩት ደግሞ በበቀል ያሳደገቻቸው እናት ሀገራቸውንና ቤተክርስትያናቸውን ሊያጠፉ እዛው ተደባልቀው በሀላፊነት ይቀመጣሉ፡ በግልጥም ከብርያል ልጆች ጋር በአንድ ማእድ ተቀምጠው የግፍ ጉድጓድን ይቆፍራሉ። የቀደመ ፍቅራቸውን ጌታ ያውቃልና

ይታገሳል፤ የዓለሙ አሳች ገዥም ልጆቹ በጌታ የጥፋት ጅራፍ እንዳይገረፉ ከወደቁት ምርጦች ጋር ይደባልቃቸዋል። በምርጦቹ ላይ ያለ የጌታ ፍቅር ጥላ ለጋኔኑንም ልጆች ጥላ ይሆናል። ለምርጦቹ የተሰጣቸው የንስሐ እድሜና የተዘረጋላቸው የፍቅር ጥላ ወደኋላ ሲያፈገፍግ አብረው ከጋኔኑ ልጆች ጋር በሦስቱ የፀሐይ ቃጠሎ ይጠፋሉ። አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት፡ አንድ የእሳት አሎሎ የሚነድ ፀሐይ ነውና የትዕግሥቱን ውቅያኖስ የሚያሞቅ፡ ሲልም የሚያፈላው የፀሐይን እንክብል በመሐል እጁ የያዘ ጎያል ነውና ጥላውን ከውቅያኖሱ ቸርነት ላይ ሲገፈው የፀሐዩ ቃጠሎ ገሃነምን ማረኝ ያሰኛል፡ የጋኔኑ ሰራዊትም በሉሲፈር ውድቀት ቀናት ወደተዘጋጀለት የሚፈላው እሳትን መርጠው ወደእዛ ይነጉዳሉ። ይህ የጌታ የክብሩ ፀሐይ ጎይል ከገሃነሙ እሳት ጋር ሲወዳደር ገሃነሙ ቀዝቃዛ ውሃ ነው፡ እኛ የሰው ልጆች የምናያት በቀትርም ግዜ የምታስጨንቀን ፀሐይ የበረዶ ክምር ናት። የሥሉስ ቅዱስ ክብር ወሰን የለውም።

የተመረጡ የቤቱ አገልጋዮች የወደቁትን ወድቀት አየሁት፡ በጸጸት የሚኖሩትን ልጆቹን ገመና የማይገልጠው ጌታ አባቶች ያዝኑላቸው ዘንድ የወደቁበትን የኃጢአት ጥልቅ አሳየኝ። ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለው ብዙ ኃጢአት ባለበት የጌታ ጸጋ ትበዛለችና የጌታ ልጆች በዘመኑ ኃጢአቶች ሰጥመው ሕይወታቸው ውስጥ የጌታ ምሕረት ጸጋና ጥሪ ከቧቸው ወደመንገዳቸው እንዲመለሱ ይለምናቸዋል። አይ የእኔ ጌታ፡

የሚለመነው ግን የማይለምነው ጌታ የልጆቹ ፍቅር አስጨንቆት መንፈሱ መንፈሳቸውን ይለምናል፡ ወደ እሱ እንዲመለሱ ግን የጋኔኑ ዘመን ለእሱ ተሰጥቷልና፡ የጸጸት መንፈስ ተነጥቆ ኃጢአታቸው እስቲገለጥ በልበ ደንዳናነት ይኖራሉና ጋኔኑ ኃጢአታቸውን በሚገልጥባቸው ወቅት ዐይነ ጥላቸው ተገፎ በድንጋጤ እራሳቸውን ያጠፋሉ። ይህ መልእክት ስለእነሱም ተጻፈ፡ ጌታ ልጆቹን ይወዳልና፡ የምንከፍለው ዋጋ ፍቅር ጸጸት እና ንስሐ ብቻ ነውና፡ ኃጢአታችሁ ቢገለጥ ጌታስ እርቃኑን በምድር ተሰቅሎ የለምን፡ የዓለም ፈጣሪ በፈጠረው ዓለም ውስጥ በፈጠረው ፍጡሩ እርቃኑን ተሰቅሎ የለምን? ታዲያ ኃጢአታችሁ ቢገለጥ ሁሉ አፈር በሚሆንባት ዓለም ምነው ከፈጣሪ የፍቅሩ ዐይን፣ የእርቃን ስቅለቱ ይልቅ የአሕዛብ ዐይን ጎይልና ያጣችሁት የመሰላችሁ ክብራችሁ በልጦባችሁ ራሳችሁን መጉዳታችሁ? ይላል የጌታ ቸርነት። ብታዉቁትስ ትልቁ የሚበልጠው ክብር በጌታ ታድሶ በደመቀ ክብር የጌታን ቸርነት መግለጥ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

ኢትዮጵያውያን ከአምላክ በራቁ ቁጥር ከአዳም ልጆች ወደ ጌታ የሚሄደው የአልፋ ኦሜጋ የምስጋናው እራት ይጎድላል። የማይርበው፤ የማይጠማው የማይጠጣው የማይበላው አምላክ እራቱና መጠጡ ምስጋና ነው፤ የኢትዮጵያውያኑም

የአምልኮ ሥርዓት መንግሥተ ሰማያዊ ነውና በኃጢአት ዓለም ውስጥ ተዘፍቀው ከሚኖሩ ሥጋ ለባሽ የጌታ ልጆች ይህ እራት ተሰርቶ ወደሦስቱ አንድ መጋረጃ ሲያርግ ለኃይላቱ፤ ለሰራዊቱ ድንቅ ነው። ይህች ሀገር ታድያ የዓለም ሰላም፤ ጽድቅና፤ ህልውና ውስጠ መሰረት ተደርጋለችና፤ ከእርሷም ጎያሉ ጌታ መሐላም ምስጢርም አለውና፤ የዓለም ፍጻሜ ቁልፍም በማህፀኗ ውስጥ ተቋጥሮ ተደብቋልና እሷ ስትረክስ ዓለም ትረክሳለች፤ እሷ ደሟ ሲፈስ የዓለም ደሟ ይፈሳል፤ ነገሩ ከእዚህም ይጠልቃል፡ ቅዱስ ዑራኤል የጌታን ደም በኢትዮጵያ ላይ ከረጨና ታሪክ የማያዉቀው የባዜን መኮንን የመጀመሪያውን የጌታን ቤት በኢትዮጵያ ላይ ከመሠረተ ጀምሮ በዓለም የፈሰሰው ደም ሁሉ የኢትዮጵያ የደሟ ዋጋ ነው ግን ወደአልታዘዝኩት አንዳልሄድ ልመለስ።

ነገሩ እንዲህ ነው፤

ሦስቱ አንድ ጌታ የኢትዮጵያን የበጎ ሕልም ፈጻሚውን የብርሃኑን ልጅ አሳየኝ፤ እሱን በአየሁበት በእዛው ቀንም በኢትዮጵያ ላይ የንጹሃንን ደም እንዲያፈስ በእርኩሰት የተወለደውን እባብም ሥልጣን በተሰጠው ሰሞን አየሁት። ደካማ ዐይኔ በአንድ ቀን ውስጥ ቀኑ ገና ሳይመሽ ብርሃንን እና ጨለማን ተፈራርቀው አየ። ትንሽም ተድላ ደስታ እንዳይሆነው ጨለማው ብርሃንን በብርሃንነቱ አላየውም ለብርሃን አልታደለምና፤ ልቡ ደንዳና፤ ጎሊናውም የተዘጋ የሲያል ጥልቅ፡

የጋኔኑ ድቅል ነውና። ብርሃኑ ግን ጨለማውን አይቶታል። የኢትዮጵያ የጨለማውና የብርሃኑ ትንቢት ፈጻሚዎች በአንድ ቦታ መገኘት የብርሃኑ ያንን ማወቅ፤ የጨለማው ያንን አለማወቅ ድንቅ ነበር። እኔ ግን ዓለም በሚያያቸው ማንነት ሳይሆን ጌታ በሚያውቃቸው ማንነት ማየቴም አለማየቴም እውብ ድንቅ ነው።

የብርሃን ልጅ የተጻፈለትን አላዳረገምና የሀገሩ መከራ ቀን ረዘመ፤ የሕዝብም ወገቡ በእምነት በእውነት በጀግንነትም አልጠበቀምና የመከራው ቀን ረዘመ። ጨለማው ከእሱ የሚጠበቀውን ነፍሱ አውቃ በትጋት ሠርቷልና እንዲያፈስ ከታዘዘው በላይ ደም አፈሰሰ፤ ከታዘዘውም መከራ በላይ መከራን በሕዝበ እግዚአብሔር ላይ አመጣ ስለዚህም የአጋንንቱ የብርያልና አስማን ድዮስ ደግሞም የሰው ልጅ ድቅል ሥጋ ለባሽ ውሕድ ጋኔን ሆኖ በአጠገቡ ያሉትን ሁሉ ለከፈ። ይህ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተንሰራፋው ጨለማ ሙሉ ሰውም አይደለም፡ በጋኔኑ ፍትወት የተፀነሰ እኩይ ነው። እንድያ ተፀንሰው በቅዱሳን ሥራ በጌታ ቸርነት ብዙዎች ተጠምቀው፡ ቆርበው፡ ከብረው አልፈዋል። አሁን ግን በዚህ ዘመን ቅዱሳኑ ከሀገርና ሕዝብ ተሰውረው፡ እነሱን ያልሆኑ ግን እነሱን መስለው በመተት የሚያታልሉ ተንስራፍተው እንኪንስ ድቅል ጋኔኑን በንስሐ ሊያድኑት ጋኔኑ የሚለክፋቸውን የሚያድኑ ካህናት ጠፍተው ጠበላት ነፍስ ዘርተው ከጋኔኑ ሠራዊት ጋር ይዋጋሉ። ይህ ድቅል ሥጋ ለባሽ ግን የተለየ ነው፡

የታዘዘው ሥራ አለው፡ ሥራውንም እየሠራ ነው። ውዳሴ ማርያም፤ ሰይፈ መለኮትን ወይም ድርሳነ ሚካኤልን ሳይደግም የጨበጠው ሁሉ በእሱ ተለክፏል፡ ክፋቱን እያየ ከእሱ ሹመትን የከጀለ ሁሉ ጸሎቱ አልበጀውም ፡ የተለከፈው ሁሉ ልክፍቱን ወደሌላው ዘርቷል። በዓለም ላይ ካሉ እርስ በእርሳቸው በብርያል ድቅል ልጅነታቸው የማይተዋወቁ በዓላማ ግን አንድ ከሆኑ ወንድማማችነታቸው በጋኔኑ የሆኑ መሪዎች ውስጥ ይህ እባብ አንዱ ነው። እነዚህ መሪዎች ሁሉ የሐሳዊው መሲሕ መንገድ ጠራጊዎችና የአዳምን ልጆች በራዥ ናቸው። ይህንን የሚያውቁባቸው ብዙዎቹ እድሜ የላቸውም። ማንም የማያውቀኝ እኔም ሰው አላወቀኝምና ደህና ነኝ ማለት አይደለም። የማጋልጠው ያውቀኛልና። የበጎ ሕልም ፈጻሚው የብርሃኑ ልጅ ግን እራሱን ገልጦ ኢትዮጵያን ወደ ጎያሉ ጌታ እንዳስባርክ፡ ብርሃንን እንዳውጅ፡ የጌታን መንግሥት በኢትዮጵያ መንግሥት እንድመሠርት የመጣሁት እኔ ነኝ ቢልም ሕዝብ ይቀልድበታል። ብርያልም በዛ ሐሴት ያደርጋል። የወደቀው መልአክ በዓለም ትልቁ ደስታው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዘኝነትና እርኩሰት ነው።

ይህ ፌዘኛ ትውልድ ንጉሡን ከእነ ቅባቱ ሌባ ብሎ ካበቃ በኋላ በዓለም የተበተነው የብርያል ልክፍቱን ይዞ አዲሲቷንም ምድር ለከፋት፡ በጋኔኑም ጭስ አዲሲቱን ሀገር አጥኖ ለከፋት፡ ይህች አዲስ ሀገር ብዙ የጌታ ልጆች አሏት ግን የአምልኮ ሥርዓቷ መለኮታዊ ተዋጊ አይደለምና መሠረቷ ተነዋወጸ።

የተለከፈው ኢትዮጵያዊ አዲሲቱን ምድር እንደለከፋት ሁሉ ደህናው ደግሞ ስለጌታ ፍቅር በምድሪቱ ላይ የመሠረተው የኢትዮጵያ አምልኮ ሥርዓት ስለአዲሲቱ ምድርም ይጸልያልና፡ በሰላምም ጌታን ይቀድሰው ዘንድ የአዲሲቱ ምድር ሕጓም ሕዝቧም መንግሥቷም ፈቅዷልና ፈጽማ እንዳትጠፋ ቃል ኪዳን ሆናት። ኢትዮጵያን ልጇቿ እየናዷት እንዳሉት ሁሉ ያችም አዲስ ሀገር ጋኔኑ በወረሳቸው በተዳቀላቸው ልጆቹ ይንዳት ዘንድ ተያይዞታል፡ ይህችም አዲስ ሀገር ምንም ኢትዮጵያውያንን ብታቅፍ በኢትዮጵያ ላይ ቆምራለችና፡ እንደ መስቀሉ ሥር ቁማርተኞች መሪዎቿ ረክሰዋልና ለአጭር ዘመን ለሁለት ትከፈላለች፡ ብዙ ደም ይፈስሳል፡ የጌታ ልጆች የጋኔኑን ድቅሎች ይዋጋሉ፡ ያሸንፋሉም። ግና ያቺ አዲስ ሃገር ሕዝቦቿ ለመረጡት ካልሆነ በስተቀር የአብርሃም ቤት መሆኗ ይቀራል፡ ጎያልነቷንም መልሳ ትረከባለች፡ አንድነቷንም ለሁለተኛ ግዜ በጌታ ማኅተም ታጸናለች፡ ለመጨረሻው የዓለም ፍጻሜ ጦርነትም ትዘጋጃለች፡ የማያሸልባቸው ልጆች አሏትና በጌታ ጎይል የገዛ ሕዝቦቿ ይቤዟታል። በውስጧም ያሉ የኢትዮጵያ ልጆች እድል ፋንታቸውን ከጌታ ልጆች ጋር ካደረጉ የአብርሃም እንግዶች ይሆናሉ፡ ከጋኔኑ ጋር ከወገኑ ግን የጋኔኑ ሲሳይ ሆነው ይቀራሉ፡ የጌታም ልጆች ሥራቸውን ከሀገራቸው ይነቅሉታል።

ግን ለምን ይሆን ኢትዮጵያ መዳን ያቃታት? ስለምንስ ይሆን የመከራዋ ግዜ ከተተነበየው የመከራዋ ቀን ሊያጥር ያቃተው?

የተማሩት ልጆቿ ጋኔኑ ላዘጋጀላቸው የሀሳብ ጣዖት ተገዝተዋልና ጣዖቱ እርስ በርስ ከፋፈላቸው፡ የተማሩት በትምህርታቸው ጣዖት ረክሰው ያልተማረውን የዋህ ድሃ፡ አርሶ መጽዋች ደሙን አፍሰው አስፈስሰው ሰዉት። የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስቷ ጣኦት አልነበረም ግን መሪዎቿ ደግ የሠሩ መስሏቸው አስቀድመው ጣዖታዊ አስተሳሰብ ያላቸውን ሃገር እንዲያሠለጥኑ ወደመንግሥት ሥራ አቀረቧቸው፤ ቀላቀሏቸው፣ ጋኔኑም ከነጓዶቹ ተደላድሎ ወደቤተ መንግሥት ገባ፤ ሀገርም እንደመሠልጠን ፈንታ ሰየጠነች።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

በኢትዮጵያ ላይ ከተነሱት ሁሉ እንደ ጥቁሩ ውሻ መንግሥት ኢትዮጵያን ያረከሰ አልነበረም። ጌታ ተክዶ፡ የጌታ ቤቱ ውስጥ እዛው አድገው ግን አስማን ድዮስ በለከፋቸው ልጆቹ ቤቱ ተዘግቶ፡ እንደተለከፉ የውሾች ልጆች የሰው ልጆች እርስ በእርስ ተባሉ፡ ምድሪቱ በደም ረከሰች። ድሮ ደም አልፈሰሰም ወይ ቢሉ አንድም የመሳፍንቱ ወግ ሆኖበት እንጂ ጋኔን ተጠናዉቶት አልሆነም፡ በአንድ ዘመንም በልብነ ድንግል ጅራፍ በግራኝ አህመድ በቀል ነው የተነሳ፡ የግራኝ አህመድ ጦርነት በተለያዩ አማኞች መሃከል ደም አፈሰሰ እንጂ ጌታን በካዱ የኢትዮጵያ መሪዎች የኢትዮጵያውያን ንጹሕ ደም በተደቀለ ንጉሥ አልፈሰሰም። ዘርዓ ያዕቆብን ባያሙት፡

ያዘዘዉንም ልጆቹ ፈጽመው ቢሆን ግራኝ አህመድም ነጋዴ ሁኖ በቀረ ነበር፡ ልብነ ድንግልም በበሰለ ነበር።

ግራኝ አህመድ የአብርሃምን አምላክ ክርስቶስን የሚያመልኩትን በሰይፍ ጎይል አስልሞ ያሰገዳቸው ወደ አብርሃም አምላክ ወደክርስቶስ አባት ነበር፤ የወሰደባቸው የመስቀሉን ሰላም፡ ለተመረጡት የተሰጠዉን የሦስቱን እውቀት ነው። ጡቁሩ ውሻ ኢትዮጵያ ላይ ያመጣባት ግን የወደቀው መልአክ አስማን ድዮስ የመሠረተው ሥርዓተ ዓለምን ነበር፡ሕዝቡን ወደጋኔኑ ደም እየገበረ አሰገደው፤ የክርስትያንን ደም ከነጳጳሱና ካህናቱ ደም ጋር፡ የእስማኤልንም ደም ከነወልዮች ደም ጋር ገበረለት። አስማን ድዮስም የኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀመጠ ብርያልም ሕዝቡን አታለለው አሰነፈው። በንጉሥ ስም እንዳይቀመጥ የኢትዮጵያ ዘውድ የተሰየመው በአሸነፈው አንበሳ በድንግል ማርያም ልጅ በዘርዓ ያዕቆብ አምላክ በጌታ እየሱስ ክርስቶስ ስም ነውና ዘውዱ ያቃጥለዋል። ያንን አለማድረግ መቻሉ ያቃጠለው ጋኔን ጨረቃ የተጫማቸው እመቤት ላይ እንደተነሳሳባት ሁሉ በእሷ ወደተመሰለችው ቤትና ሲኖዶስ ቁጣውን ሰደደ፤ መስቀሉ ሃይላቸው እንደሆነ የረሱ፡ እንደ መጥምቁ ቆራጥ መሆን ያቃታቸው ቀሚሳቸውን አስረዝመው ጽድቃቸውን ያሳጠሩት ጥቁር ለባሾች ግን የልባቸውን በር ከፍተው አስገቡት፡ በእነሱም ልብ አድርጎ ወደ ጌታ ቤት ገባ።

የእርኩሰቱን መሃላ በተጠናወታቸው አባቶች ጣት፡ በቅዱስ ሲኖዶሱ ወለል ላይ አተመው። መነኩሴውን አባት እንደ ቀያፋና ሃና አሳልፈው ለጋኔኑ ሰዉት። እሱም ቀድሞት የተሰዋውን የኢትዮጵያን አባት ተከትሎት ሄደ። የንጉሱም ወታደር ንጉሡን ክዶ እንደ ገደለው ሁሉ ጳጳሳቱም ሊቀ ጳጳሱን ክደው አሳልፈው ለእርድ አቀረቡት። ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ክህደትና እርግማን እንደገባ ሁሉ ቤተ ክህነቱም ውስጥ ግፍ ገባ። በንጉሡ ወንበር እስተአሁን ድረስ የጋኔኑ ልጆች እየተፈራረቁ እንደቀለዱ ሁሉ፡ በጳጳሱም ወንበር ላይ ትሕትና ጎድሎ የጋኔኑ ልጆች እንደ ሕፃን ልጅ በሚያፈዝባቸው ጳጳሳት አፈዘበት። የጸጋ ዘአብ ልጅ ዳግማዊው ኤልያስ አባታችን ተክለሃይማኖት ለእኔ አይገባኝም እያለ ግን በሕዝብ ተማጥኖ ለመንፈቅ የተቀመጠባትን ወንበር፡ የመንፈስ ልጁ በጥቁሩ ውሻ በአስማን ድዮስ ዘመን የተሾመው ዳግማዊው ተክለሃይማኖት በትሕትና እያለቀሰ የተቀመጠባትን ወንበር እነዛ ሁለት ጳጳስት ግን ሕፃናት የጣፈጠ ህብስትን እንዲሻሙ እነሱም ወንበሩን ተሻምተው፡ አንዱም እንኪን እኔ ልነስ ጌታ ይክበር ብሎ መልቀቅ አቅቶት፣ እራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል የሚለዉን ወንጌል ንቆ፡ በማነስ ውስጥ መተለቅ መኖሩን ረስቶ፡ ለሁለት ተቀመጡበት፤ ጋኔኑም በደስታና በፌዝ ፈነደቀ። ትሕትናን በቤተ ክህነቱ እንደገደለው አይቶ ከተፈጠረ ጀምሮ ተደስቶ ከሚያዉቀው በላይ ልቆ ተደሰተ፡ ጌታና ቅዱሳኑ በትሕትና ጦር ነበርና ይህን አሳች መንፈስ ሲያሳፍሩት የኖሩት የትሕትናውን መንበር የሸሚያ መንበር

ሲያደርጉት ምንኛ ይደሰት። ጌታን ሲያስደስት የኖረው የተክለሃይማኖት መንበር ጋኔኑን ለማስደሰት በቃ ስለዚህም የቤተ ክህነቱ ወንበር በሰው ፊት ክብር የሚመስል ግን የተናቁበት ለነፍሳቸውም ጭንቀት ሆነባቸው፡ አርፈውም የማይጸልዩበት ሆነባቸው፡ ደለቡበት እንጂ አልጸደቁበትም፣ ዳዊት ደነደኑ እንዲል። ጋኔኑ ቴዎፍሎስን ሲያሳንቀው አልተደሰተም ወይ ቢሉ፡ ያ የሥራ ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አልነበረም፡ ጋኔን ጨርሶ ዳር ባላደረሰው ሥራ አይደሰትም፡ መነኩሴውም በትህትና ንስሐውን ተቀብሎ ሰማዕትነትን ተቀበለ፡ ጊዮርጊስን መሰለ እንጂ በሽንፈት አልሞተም፡ እሱን የተካውም ቢጫ ለባሽ፡ እጅግ የከበረው መነኩሴ ጌታ በእሱ ላይ አድሮ የልጆቹን ቤት ሊባርከው፡ ፈጽሞም እንዳይጠፋ ቢፈልግ ተክለሃይማኖትን በተክለ ሃይማኖት መንፈስ ጠርቶ ሾመው፡ ይህም ጻድቅ ጽድቅን ሰርቶ በበዛ ጽድቅና ትሩፋት ስሙን መስሎ አለፈ፡ ፈለሰ። ታድያ ያ ጋኔኑን ምን ያስደስተዋል? ሥራውን የጀመረለትን፡ ሀገር ያፈረሰለትን፡ የጌታን ቤት የዘጋለትን ትጉህ ሥጋ ለባሽ ጋኔን ያን ጥቁር ውሻ ከነጻጻሱ ዞር አድርጎ፡ በተንኮላቸውና በሥጋቸው ምርጫ በውስጣቸው ገብቶ የነገሠባቸውን ተንኮለኛውን ጠይም ዘንዶ ይሁዳንና ነጭ ለባሽ ሐዋርያ መሳዩን ሐናንያን አንድ ላይ አምጥቶ ሹሞ ሸልሞ ሥራውን ቀጠለ፡ ሀገርን አቆሸሸ፡ ትውልዱን ፈጽሞ በከለው፡ ለጥቆም አዋረደው፡ አብዝቶም በዝሙትና በሱስ አሠለጠነው። ጌታም የሳሙኤል ዋልድባን ልቅሶ ሰምቶ ከጋኔኑ ላይ ይሁዳንና ሐናንያን አንድ ላይ

ቢነጥቀው ቀድሞ የተዘጋጀበትን ተዛና ተዚህ ከሥጋው አዳቅሎ ወልዶ ያዘጋጀዉን ሌላ ድቅል ሥጋ ለባሽ ጋኔን ልስልስ ያማረ ቆዳ ያለዉን እፉኝት እባብ ወደ ዙፋን አመጣው። ይህም ሥጋ ለባሽ ጋኔን እንደ እፉኝት ቆዳውን አሳምሮ እንደ ጋኔኖቹ አለቃ ሉሲፈር እጅግ አታላይ፤ መንገዱም ፈጽሞ የረቀቀ ሁኖ ገነነ። ከአንዳንዶች በስተቀር የጨበጡት ሁሉ ግን ተለከፉ። አጥብቀው የሚጸልዩት ተቋቋሙት፡ ከርሳቸውን የመረጡ ሁሉ በእሱ ምክንያት ከረፉ። ጌታ ግን የጨለማው መጨረሻ ሊያደርገው ፈቅዶ ጥበብን ነጠቀው፡ የዚህ ሥጋ ለባሽ አባትም በኢትዮጵያ ላይ ትንሽ ግዜ እንዳለው አውቆ የማይጠግ የሚመስል ጥፋትን በሃገሩ ሁሉ ዘራ። ሕዝብም ደንቁሯልና ጥፋቱ አልታይ ብሎት በእባቡ ተንኮል በሐናንያ ልጆች ልበ ደንዳናነት በአርሶ መጽዋቾች ሞኝነት የቆራቢ ልጅ የቆራቢን ልጅ፡ የካህን ልጅ የካህንን ልጅ አረደው ገደለው፡ ያ ልስልስ እፉኝት እባብም ወፈረ፡ ደነደነ፡ መርዙ ተዝረከረከ፡ መርዛም ዘንዶ ሆነ፡ ቆዳዉም አንድ መልክ ሆነ፡ ቀንዱም ተገለጠ፡ ከጭራውም መርዝ አለው፡ ከምላሱ ካለው ይልቅ ከጭራው ያለው መርዝ ይበረታል፡ ጭራውም ሌላ የእባቡ ታናሽ እራስ ሆነ፡ መልክም ኖረው፡ ከዋናው እራስ ይልቅ ይህ እራስ ደም ጠጪ ጋኔን በውስጡ አለው፡ የሕጻናትን ደም ካልጠጣ ያንቀዠቅዠዋል። ዋናው እራስ ደም ያፈሳል፡ ይሄኛው እራስ እነጠቋርን በውስጡ አቅፎ ደሙን ያለለከት ይጠጣል። ይህ ከጅራቱ የበቀለው እራስ ልዩ ምልክቱ የሰውነቱ ክርፋት ነው። የደጋጎች ሕጻናትን ደም በውስጡ የተዋሐደው ጋኔን ጠጥቶ

ሊጠግብ አይቻለዉም። ዋናውን እራስ ስትቀጠቅጡ ይህን ጅራት መቁረጥ እንዳትዘነጉ፡ ይህ ጅራት ብዙ ደም ሊጠጣ ገና ዘመን አለውና በጸም በጸሎት ቀጥቅጡት፡ እንደ ቀንድ አውጣ ይቀልጣል።

ወደቀደመ ነገራችን ልመለስ፡ በጽዮን ስለሆነው ነገር፡

ይሁዳም ከታላቅ ነገድ ወጥቶ ታናሽ እንደሆነው ሁሉ የይሁዳው ካህን የሐናንያ ልጆች የታላቆች ዘር ሳሉ እራሳቸውን አዋርደው የሰጲራ ልጆች ሆኑ። የጽዮን ልጆች ጽዮንን ክደው ሐናንያን ከቤተ ክህነት ቀላቅለው አግብተው እምነትን ሃይማኖትን በሀገርና በቤተ ክህነት ላይ አጎደሉ፡ ባዕዱ እምነት ጣዖት ሆነባቸው። ያንን ጣዖት ከሃይማኖታቸው ጋር ቀላቀሉት። የቀደመ ፍቅራቸውን፡ የእናቶቻቸውን እመቤት የአባቶቻቸውን ጌታ በጣዖቶቻቸው ለወጡት። የጣዖታቸው ካህናት የህልውናቸው ሐሳውያን ነብያት ሆኑባቸው። ልጆቻቸውን ገበሩባቸው። የልባቸው ድንዳኔ የዲያብሎስ ትዕቢት ሆነባቸው። የመከራ ሱባኤን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዋዜማ ጀመሩ፡ ይሁዳ ትንሣኤን ከሐዋርያት ጋር ለማየት እንዳልታደለ ግን ትንሣኤ ያለሞት የለምና ጌታን ለሞት ሰጥቶ በልቡ ድንዳኔ የሰጠበትን ገንዘብ በትኖ እንደሞተ ሁሉ ጽዮንን በሐናንያ ለውጠው ኢትዮጵያን ሸጠው ለውጠው፡ ለእባቡም አሳልፈው ሰጥተው፡ በልባቸው ድንዳኔ ግድ ብለው ራሳቸውን ሰቅለው ከትንሣኤ ጎደሉ፣ የሰበሰቡትንም እንደ ይሁዳ

አባታቸው በተኑ። ግና መከራቸው ስለጽዮኗ እመቤት ርኅራኄ ያጥርላቸው ይሆን? ጌታ ያውቃል፡ አሜን ይጠርላቸው። ከብርሃኑ ጋር የሚመጣው ባሕታዊ ይጸልይላቸዋል፡ ካከበሩት መከራቸው ያጥርላቸዋል ግን ለምዕተ አመት ኃጢአታቸውን የሚያስታውሳቸው የጎን ቁስል ታዞባቸዋል። ያ ቁስል ስለእነሱ የልብ ድንዳኔ ገና ከጥንት በደጉ ምኒልክ ካህናትን መኳንንትን ሳያማክር በሠራው ጥፋት የተፈጠረ በሽታ የሚመስል መድኃኒት ነው። ያንን በሽታ መሳይ መድኃኒት አትንኩት፤ ጌታ እስቲሸረው ይኑር።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

አባቶች በሱባኤ የአቡነ ቴዎፊሎስን አምላክ ይቅርታ ካልጠየቁ፡ ጥቁሩ ውሻ መነኩሴውን እንዲገድል፡ የመነኩሴውን የከበረ በድን እንዲያዋርድ ፈቅደዋልና አሁን በሲኖዶሱ ወለል ላይ አስመጥተው እንደ ጻድቁ ይምርሃነ ክርስቶስ መቃብር በዙሪያው ከበው በጌታ ስም የመነኩሴውን ነፍስ ይቅርታ ካልጠየቁ መርገሙ ከቤቱ አይወጣም። የተደረገውን የሚያውቅ ያውቃልና፡ እንኪን የግድያውን ግፍ፤ የአቀባበሩን ስድብ የሚያውቅ ያውቃልና፤ ይህን እርኩሰት እንዳልጽፈው ለጣቶቼ ከበደኝ። አቤት ክፋት፡ አቤት ድፍረት፡ አቤት መታወር፡ አቤት እርግማን። በእዛ ግፍ ኢትዮጵያና ቤተ አምልኮዋ ታውረው ቀሩ። የእዛ ሲኖዶስ ወለልን ከረገጡ ሁሉ

ከጣት ቁጥር ያነሱ ናቸው የመርገሙ ጨርቅ ያልነካቸው። ከእነዛ አንዱ ከእሳቸው በፊት ከመጡት ከፀጋ ዘአብ ልጅ በስተቀር እና ከእሳቸው በኋላ ከመጡትም ሁሉ ጳጳሳት በላይ የሆኑት ርዕሰ ጳጳሳቱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው። እያለቀሱ ተሹመዋልና፡ ስልጣናቸውም ቀምብራቸው ነበርና፡ ለደመወዛቸው ሳይሆን፡ ለወንበራቸው ሳይሆን ስለሕዝብ ከጥቁሩ ውሻ መንግሥት ከጋኔኑ ልጅ ጋር ተፋጠዋልና መርገም ሳይነካቸው ወደ ጌታ ሄዱ፡ በረከታቸው ይድረስን። አሜን ይሁን ይሁን ይሁን።

እንግዲህ ይህ ታልሆነ፡ የመከራው ብዛት፡ የአባቶችም ቀጣይ ውርደት ይቀጥላል፡ በእነሱም ምትክ ልጆች ይወለዱላቸዋል፣ ጽዋው እስቲሞላ።

ብርሃኑን ይዞ ሊመጣ ያለውም የብርሃኑ ልጅ ወደጌታ ሥጋና ደም አልቀረበምና፤ እውቀቱ ሳለው፤ ማን እንደሆነ እያወቀም አልቀረበም። በመሰዊያው ፊት ሳይነግሥ እንዴት ለሕዝብ ይንገሥ? የሕዝቡ ኃጢአት እጅ እግሩን አሰረው። የአለም እውቀት በዝቶለት፡ የመንፈሳዊው ዓለምም መስኮት ተከፍቶለት ሳለ፡ ቅባቱ ተንጣሎለት ሳለ ሰነፈ፡ ወሰለተ። ህዝቡም ክፋቱ በዝቶ እንዴት ሊነግሥ ያለውን ይወቀው? ተወልዷል፡ ሕዝብ አይቶታል፡ እሱም ስለደካሞች ድምፁ አስተጋብቷል፡ ጌታ ዓለሙን አስመስሎት፡ አመሳስሎት

አኑሮታል። ብዙዎች የማያዉቁት እጅግ በትህትና የከበረ በሶስት ሱባኤ ያህል እድሜ የሚበልጠው እንደራሴም አለው። እንደራሴው በአሕዛብ ዓለም በጌታ መሠዊያ ፊት ከብሮ እየጠበቀው ነው። ብርሃኑ ግን መሠዊያውን ፈራው፡ እንደ ነብዩ ኤርምያስ ከንፈሩ አፈወርቅ እንደመሆን ፈንታ ጌታ ያደረቀውን ቅጠል መስሎ ብርሃኑ አልበራ አለ። እንደአመድ ፍሕም አልበራ አለ።

ይህ የብርሃን ልጅ ብቻውን አልተወለደም። የእሱ እኩያ የሆነ አብሮ ተወልዶለታል፡ ሌላም እሱንም ወደወንበሩ የሚያደርሰው ከእሱ ቀድሞ ተወልዶለታል፡ ይህም ቀድሞ የተወለደው መጀመርያ በወንበሩ ይቀመጣል፡ ሕዝብ ያምነዋል ይወድደዋል፡ ለብርሃኑ ልጅም ቤቱን ይጠርግለታል፡ ያፀዳለታል። ቀለበትም ይሰጠዋል። ለኢትዮጵያም ሕዝብ ይህ ከርታታ ሌሊቱን ያነጋለታል፡ የንጋቱ ጀንበር እንደ ኖህ ቀስተ ደመና ለኢትዮጵያ የምህረቷ ኪዳን ይሆናል። የብርሃኑንም ልጅ ከሱባኤ በኋላ ለሕዝብ ይገልጸዋል። እሱም በሰላም በቤቱ ከዘመናት በኋላ ያርፋል፡ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለኢትዮጵያ ሊጨብጥላት እንደ ንስር ሲበር፡ እንደ ፈረስ ሲጋልብ፡ ሲባክን ኖሮአልና፡ በበረሃም እንደ ዮሃንስ ብርሃንን ሊገልጥ ይንከራተታል። ይህ ሰው ፍጹም የከበረ ነው። አንዱ አብሮ የተወለደለት እኩያው ደግሞ አሁን መነኩሴ ነው፡ ንጹሕ ነው። አለም አልሸለመውም፡ የሚጎትተው ያማረ ቀሚስ የለውም፡ መልኩ ዮሃንስን ይመስላል፡ አይቸዋለሁ፡ በአይነ ኅሊናም

በሥጋም አይቸዋለሁ፤ እጁን ጨብጬአለሁ፡ የከበረ የብሕትውና ጡረኑን አሸትቼአለሁ። ጽድቁ ልብን ይሰልባል፡ የወርቅ መስቀል የለውም በላቡ የጠቆረች ግን በጨለመው ዓለም የምታበራ፡ ከተፈቀደለት አይን ውጭ ብርሃኗን የማያይ የከበረ እፀ መስቀል በእጁ አለ፡ ማንም ቢያየው ጌታ ከፈቀደለት በስተቀር በላዩ ላይ ያለ ሰማያዊ ክብር ላይታየው ድብቅ ነው፡ የዋህ ነው፡ ትሑት ነው፡ ከሲታ ነው፡ ጓደኛው ነብር ነው፡ ነብር አብሮት ይተኛል፡ ጋኔኑ መጪው ንጉስ እሱ ነው ብሎ አምኖ ነበር ግን እሱ በአቡነ አረጋዊ መንፈስ የሚመጣው የተክለ ሃይማኖት ወራሽ ነው፡ ጋኔኑ ሊገድለው ሞክሮ ነበር ግን በአንዲት ዉዳሴ ማርያም የጋኔኑን ጎይል ገለባበጠው ግን አልተመፃደቀም፡ ሥጋ ለባሽ ጋኔንን በአስማት አሠልጥኖ አስማን ድዮስ ላከበት ግን ያን ሁሉ በውዳሴ ማርያም ብቻ አስማቱን ሽሮ ሥጋ ለባሹን ገደለው። ይህ ዮሃንስን የመሰለ ብርቱ ደካማ አልተመፃደቀም፡ እንደውም ለጠፋው የሥጋ ለባሹ ጋኔን ነፍስ አለቀሰ። የብርሃኑ ልጅ ጳጳስ፡ የተክለ ሃይማኖት ምትክ፡ መጭው ቢጫ ለባሽ እሱ ነው። የብርሃኑ ልጅ ቦታውን ሲይዝ ይህም ትሑት ብርቱ ደካማ ወደቦታው ይመጣል፤ ሀገር ይባርካል፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እግዚአብሔር ይፍታህ ብሎ ከማሰሪያው ይፈታዋል። የቁልቢው ራስ መኮንን ትውልድ ከወንበሩ ቀንበር ከዙፋኑ ሸክም ያርፋል፡ ሳያውቅ ታውሮ ጣኦትን ወደዙፋኑ አምጥቷልና፡ ትውልዱ በዘርዓ ያዕቆብ እመቤት ላይ የወንዝ ጎርፍ የለቀቀባትን ተቀላቅሏልና ዙፋን ከትውልዱ ወጥቷል ፡

የወገኑ ትውልድ ግን ይገናል ግና የመከንን ትውልድ ላይ አፉን የሚያላቅቅ አይኑር፡ መከንን ታላቅ ነበር፡ እንደከበረ አለፈ። ልጁም ታላቅ ነበር፡ አንሶ ነበር ዳግመኛ ግን በሞቱ ተልቆ ወደ አባቶቹ ተቀላቅሏል። እንዲከብር ዙፋኑን እንዲወርስ የሆነው ለጌታ ቤት ብርሃን ሆኖ ሳለ ብርሃኑን ለተነጠቀው ልጁ ነው። የአባቱ የነዓኩቶ ለአብ በረከተ ጽድቅ ይምራው፡ ብርሃን ይሁነው፡ አምላከ ነአኩቶ ለአብ አንተ ምራኝ ይበለው።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

የኢትዮጵያ ህልውና የተዋሕዶ ደጅ፡ ምስጢራቸውም ለአዲሱ ትውልድ ዋዛ ፈዛዛ ነው፡ ሽሙጥ ነው፡ ማሸሟጠጥም የታላቅነት ምልክት ሆኖ ክብር አግኝቶአል። አሸሟጣጮም፤ የተመረጡትንም ለሽሙጥ አሳልፎ የሰጣቸውም የሚሰጣቸውም ሁሉ የትንቢት መፈጸሚያ ነው። ንቁ ተመለሱ። የአሸሟጣጮች ጨለማ ደርሷል፡ የተዋረዱትም ሊከብሩ ክብር ከደጃቸው ቀርቧል። ዝቅ ብለው የኖሩት ከቀደመ ክብራቸው በተመለሱ ግዜ ክብራቸው የማይፈቅድላቸውን አድርገው፡ በቀልን መልሰው ቅለትን እንዳይቀሉ፡ እንዳይረክሱ ይጠንቀቁ፡ የንጹሓን ሕፃናትን ደም በግፈኞች አባቶቻቸው ኃጢአት ምክንያት እንዳያፈሱት ይጠንቀቁ። ይህ የአሕዛብ ሥራ ነውና ጣአትን ይንቀሉ እንጂ ሕፃናትን አይንቀሉ፡ ሕዝብን ያስተምሩ ይገሥጹ ይቅጡ እንጂ ደሙን አያፍሱ። ጣአቱን ከቦታውም ከሰዉም ልብ ሲነቅሉት

ሕዝቡ ገራም ይሆናል፡ ብርሃኑም ይታየዋል፡ አስተምሩት፡ ትሕትና እና ይቅርታ ያላስተማረውን ግን እንደ ጣኦቱ ንቀሉት። ጌታን የፈራ ያከበረ እንጂ አምላከ ጊዮርጊስ የሠራውን ሰው የገደለ አይጸናምና ግና ግና ትሕትና እና የጌታ ምህረት ያልመለሰው የጌታን ሥራ ከማፍረስ አይቦዝንምና ይነቀል። ጌታ ፍሬ ያላገኘበትን እንደነቀለው የጊዮርጊስ አምላክ የሚጸየፈውን ጎፈሬ ጣኦት ይንቀሉት፡ ነቅለውም ወደ ርዕሰ ቅዱሳኑ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግዳይ ባሕር ይጨምሩት። ጌታ ሦስቱ፡ ሦስቱም እሱ አንድ ጌታ ነው፡ ይህም ርዕሰ ቅዱሳን በዘባኑ ሦስቱን ተሸክሟልና፡ ኪሩቤልን ሆኗልና ጣኦቱን ወደእሱ ግዳይ ጨምሩት፡ ጣኦቱም ጋኔኑም ይደፈቁ፡ በየአመቱም በመጋቢት አምስት ቀን የርዕሰ ቅዱሳኑ ታቦት በሃይቁ ዙርያ ይዙር፡ የማዕጠንቱም እምነት በሃይቁ ይበተን። ታቦተ ሕጉም ጣኦቱ በተነቀለበት ቦታ ቆሞ ኢትዮጵያን ይባርክ ኢትዮጵያም ከጣኦቱ ጋኔን ጦስ ታርፋለች፡ አስማን ድዮስና ብርያል ግን አያርፉምና፡ ካላቸነፉ ሉሲፈር ይቀጣቸዋልና ጦርነቱ ይቀጥላል። ግን የንጹሓን ጌታ ይመስገን ጦርነቱን አባቶች ተረክበው ይዋጉታል፡ ሕዝብ ያርፋል፡ ሀገር ታርፋለች፡ ቅዱሳን ወደመጨረሻው ዘመን ጦርነት ይሸጋገራሉ። ወደተወለዱበት ምክንያት ይተማሉ። የሰው ልጅ ዐይን የማያየው ፍጹም ጦርነት በአየራቱ ላይ ይሆናል።

ጋኔኑ አስማን ድዮስ ከሕዝብ ተነቅሎ ከአባቶች ጋር ሲዋጋ ብርያል ይደክማል፡ ምልክቱም በኢትዮጵያ ላይ የሰዶማውያን

መንፈስ ይታሰራል፡ ጨረቃን የተጫማችዋ ደግ የጌታ እናት ላይ የሚፈሰው የስድብ ወንዝ ይገደባል፡ የመሸገበት ቤቱ ከኢትዮጵያ ምድር ላይ ይናዳል፡ እንደታዘዘው ደግሞ ዓባይ ወደ ግብጽ ይፈሳል፡ ሃገር ሰላም ይሆናል፡ ወንዱ ሞገስ ሴቱም መልክ ይኖረዋል። በረሃው ይለመልማል፡ የሃገሩም ውሃ ለሃገሩ ሰው የውስጥ ጤና የቤት በረከት ይሆነዋል፡ መርዙ ከሕዝቡ አካል ይነቀላል። እስማኤል ከያዕቆብ ፍቅርን ይመሰርታል። ለኢትዮጵያ የአቸነፈው ይሁዳ ዘውድ እንደሚጭነው ሁሉ ለኢትዮጵያዊው እስማኤልም ከሰሜን ምስራቅ ንጉስ ይሾምለታል፡ በኢትዮጵያ ላይ ያዕቆብና እስማኤል አብርሃና አጽብሃ ይሆናሉ፡ የአንዱ በረከት ለአንዱ ሞገስ ይሆነዋል። ዓለም ይደነቅባቸዋል። የፍቅር ጌታ የመብአፅዮን አምላክ ሕፃኑ እየሱስ በኢትዮጵያ ዘውድ ላይ ይከብራል።

ይህም የዘርዓ ያዕቆብ እመቤት የደብረ ምጥማቋ ቅድስት ድንግል ማርያም ማደርያ ደብር ስትመረቅ የአስማን ድዮስ አከርካሪ ተመቶ የኢትዮጵያ ወገቧ ይለመልማል። ስለዚህም ኢትዮጵያ አማጠች፣ ምጥ፣ ኢትዮጵያ ማቅ ለበሰች ፣ማቅ፣ ደብረ ምጥማቅ ስትመረቅ ልደትና ትንሳዔ ሆነ። ሕዝብና የትንሳኤዋ አምጭ ወቶአደሮች ከዛ በኋላ የሰኞ ውዳሴ ማርያምን፡ ሰላም ለኪን፡ ለገቦኪን፡ ጐሥዐ ልብየን ከዘየጎድር ጋር አጣምረው ዘወትር ይጸልዩ፡ የኢትዮጵያ ትንሣኤም አብሮ ከደብረ ምጥማቅ ጋር ተመሥርቷልና የኢትዮጵያ ትንሣኤዋ

እስቲገለጥ፡ ከተገለጠም በኋላ ሕዝብና ወቶአደር እነዚህን ጸሎቶች አያቋርጡ።

ይህን የመውጊያ ብረት የተቃወመ ጌታ አይለመነው።
ኢትዮጵያ ለአራሽ መጽዋች፡ ለቀዳሽ ተኪሽ ተሰጥታለች።
ይኸው ነው።

ይህ ደግሞ ቀጥሎ የተሰጠው ጸሎት እባቡ እስቲነቀል ብቻ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

የብርሃኑ ልጅ ወደተወለደበት ምክንያት እንዳይመጣ ከመንበሩ አልቀርብ ብሎ ስንፍናን በሰነፈበት በወሰለተበት ወቅት፡ ተንከለኛው ጋኔን እጅግ በተንኮሉ ሰልጥኖ ደንድኖ የተመረጡትን የጌታን ልጆች ሎሌው ባደረገበት ሰዓት ሕዝበ ክርስቶስ ወደ ጋኔኑ ልጅ ምስልና ቤት አቅጣጫ ጣቱን ቀስሮ ዘወትር ይህን እንዲፀልይ ይሁን። በዚህ ጸሎትም ሐሰተኛው የአስማን ድዮስ ልጅ ከነሎሌዎቹ ይደመሰሳል፡ ለንስሐ የሚበቃ የእባቡ ሎሌ ካለ የታደለ ነው። ስለዚህ መልእክት ሰምቶ፡ አንብቦትም ንቆ የተወው የተናቀ ይሁን። የአሳቹ እባብ ሎሌ ጥፋት ከጋኔኑና ከእፉኝት ልጁ ጥፋት ይልቃል፤ ዳንኤልን ከአናብስት የታደገ ጌታ ጋኔኑን ሊያደቅ ከሚልከው መልአክ

አይታደገውምና፡ መልአኩም ቀድሞ አስማን ድዮስን በደመሰሰበት ብርሃናኤል በተባለው ስመ አምላክ ሰይፉን ከአፎቱ ሲመዝ አስማን ዲዮስና ድቅል ዘር ማንዘሩ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ይረግፋሉ። የእባቡ ሎሌም ቀድሞ በጌታ ቤት ከብሮ ሳለ በሎሌነት ቀሏልና፡ የጌታ ልጅ ጌታ የልጅነት ሥልጣንን ከሰጠው በኋላ ለጋኔኑ ልጅ ሎሌ ሆኗልና ጥፋቱ እጅግ የከፋ ነው። የእባቡ የጋኔኑ ሎሌ የሆነ ሁሉ ይህ መጽሐፈ መልእክት ታትሞ እጁ ከገባ በኋላ በሎሌነቱ ቢቀጥል የጌታ ምሕረት ትራቀው። ይህም መልእክት እውነት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ምልክት ተሰጥቷል። የጋኔኑን ልጅ አሳቹን የሰው ድቅል እባብ ልትጨብጡት ላላችሁ በቅርቡ የሆናችሁ የዘርዓ ያዕቆብ እመቤት ልጆች "*የድርሳነ ሚካኤል፣ የድርሳነ ገብርኤልን እና የድርሳነ ሩፋኤል አቃቤ ርዕስ አስማቶቻን*" ደግማችሁ፡ "*ብርሃናኤል*" የሚለውን የከበረ ስም አርባ ዘጠኝ ግዜ ብላችሁ "*እናንተ የጌታ መላእክት ጋኔኑን አጋልጡት አድክሙት ከነልጁ ቅሰፉት*" ብላችሁ በመዳፋችሁ ላይ እንትፍ ብላችሁ በዛው ቀን ማንንም ሳትጨብጡ በኅሊናችሁ ደጋግማችሁ "*ብርሃናኤል*" እያላችሁ እጁን ብትጨብጡት ዐይኑንም እያያችሁ በልባችሁ "*በብርሃናኤል ስምከ ቅትል ዝ እኩይ ጋኔን*" ብትሉ አይኑ ይቀላል፡ ይንቀዠቀዠል፡ ታሞም ማቅ ለብሶ ያድራል፡ ከዛ በኋላ ፍጹም በሥጋም በነፍስም ይኮስሳል፡ ይወድቃልም።

የበረታ ለሶስት ሱባኤ የደከመ ለአንድ ሱባኤ በየቀኑ በቀን ሶስትም ሰባትም ያህል ይህን ፀሎት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ጋኔኑ ልጅ ወደእባቡ አብይ አህመድ ወደጅራቱም ሽመልስ አብዲሳ ምስል ወይም መኖርያ ቤት ጣቱን ቀስሮ ያድርስ፡ ከአሳቹ እባብ መወገድ በኋላም ሀገር መሪ፣ ዳኛ መርማሪ ቢበድል፡ ፍትህ ቢያጎድል፡ ተመክሮ አልሰማ ቢል የተበደለ ድኻ ወደዚህ ጸሎት ይዙር፡ ጌታ በዳዩን ዞር ያደርግለታል፡ ግና በደም አፍሳሽ በፍትሕ አጉዳይ እንጂ ይቅር ሊባል በሚችል የግል ጠብ፡ ቂም፣ሊመከርም በሚችል ሹም ላይ ይህን ቢጸልዩ በረከት ይነሳል፡ ጽድቅ ይነሳል።

ጋኔኑን ከእነ ጅራቱ ልጆቹና ሎሌዎች ልትነቅሉ ይህን በሉ

"አቤቱ፥ ኢትዮጵያን የሚበድሉትን በድላቸው፥ የሚዋጓትንም ተዋጋቸው። ጥሩርና ጋሻ ያዝ፥ ሕዝበ ኢትዮጵያን ለመርዳት ተነሥ። ሰይፍህን ምዘዝ ድሃን የሚያሳድዱትንም መንገዳቸውን ዝጋ፤ የሕዝብህን ነፍስ መድኃኒትሽ እኔ ነኝ በላት። የድኻን ነፍስ የሚሹ ሁሉ ይፈሩ ይጐስቁሉም፤ ክፉትን በኢትዮጵያ ላይ የሚያስቡ ይፈሩ ወደ ኋላቸውም ይመለሱ።

በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይሁኑ፥ የእግዚአብሔርንም መልአክ ንጉሣቸውን ከነሠራዊቱ ያስጨንቀው።

የአሕዛቡ አለቃ ከነሠራዊቱ መንገዱ ዳጥና ጨለማ ይሁን፥ የእግዚአብሔርም መልአክ ያሳደው ድኻ አሳደ፧ልና። ሕፃናቱን አረጋውያኑን በከንቱ ያጠፋ ዘንድ ወጥመዱን ሸሸጎ አድብቷልና፥ የካህናቱንም ነፍስ በከንቱ አበሳጭቷልና፥ ደሙንም አፍሶ ተደስቷልና፡ ስላቁም ከህዳናቱ ደምና ከራሄል እንባ ጋር ወደላይ ከፍ ብሏልና።

ያለወቀው ወጥመድ ይምጣበት፥ የሸሸገውም ወጥመድ ይያዘው፤ በዚህ ወጥመድ ውስጥ ከነሠራዊቱ ከነሎሌው ይውደቁ። ኢትዮጵያ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይላታል፥ በማዳኑም ሐሴት ታደርጋለች።

የንጹሃኑ አጥንት ሁሉ እንዲህ ይሉሃል። አቤቱ፥ እንደ አንተ ማን ነው? ችግረኛን ከሚቀማው እጅ፥ ችግረኛንና ድኻውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህ። የክፋት ምስክሮች ተነሡብን፥ የማናውቀውንም በእኛ ላይ ተናገሩ። ስለ በጎ ክፋትን መለሱልን፥ ነፍሳችንንም ልጆችን አሳጡአት።

እኛስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስን፥ ነፍሳችንንም በጾም አደከምናት፤ ጸሎታችንም ወደ ብብታችን ተመለሰ። ለወዳጆቻችን ለወንድሞቻችን እንደምናደርግ እንዲሁ አደረግን፤ ለእናቱም እንደሚያለቅስ ራሳችንን ዝቅ ዝቅ አደረግን።

በእኛ ላይ ተሰበሰቡ ደስም አላቸው፤ ግፈኞች በኢትዮጵያ ላይ ተሰበሰቡ እኛም አላወቅንም፤ ሀገረ እግዚአብሔርን ቀደዷት አልተዉአትም። ፈተኑን በሣቅም ዘበቱብን፥ ጥርሳቸውንም በሕዝበ እግዚአብሔር ላይ አንቀጫቅጩ።

አቤቱ፥ እስከ መቼ ድረስ ታይልናለህ? ነፍሳችንን ከክፉ ሥራቸው የተረሳች ሀገርህንም ከተኩሎች አድናት፡ ተኩሎቹን ከእነ ልጆቹ የሚሰብራቸውን አንበሳ አስነሳ። አቤቱ፥ በታላቁ ጉባኤ ውስጥ ኢትዮጵያ ትገዛልሃለች፥ በብዙ ሕዝብ ፊት በዓለም መንግስታት መካከልም ኢትዮጵያ ታመሰግንሃለች። ትመሰክርልሃለችም።

በግፍ የሚጠሉን በላያቸን ደስ አይበላቸው፥ በከንቱ የሚጣሉንም በዓይናቸው አይጠቃቀሱብን።

ለእኛስ ሰላምን ይናገሩናል፡ እንደአባታቸው አሳቹ ሳጥናኤልም በሐሰት ሰላምና ፍቅር ይሳለቁብናል፥ በውጣም ሽንገላን ይመክራሉ። አፋቸውንም በእኛ ላይ አላቀቁ፤ እሰይ እሰይ፥ ዓይናችን ስደታቸውን፡ ሞታቸውን፡ አየው ይላሉ።

አቤቱ፥ አንተ አየኸው፤ ዝም አትበል፤ ቸል አትበል፣ አቤቱ፥ ከኢትዮጵያ ከህዝቧም አትራቅ።

ፈጣሪአችን ሰሙራኤል፡አምላካችን ምናቴር፡ ጌታችን አብያቴር፥ ወደ ፍርድ ተነሥ፥ አቤቱ፥ ፍርድህን በአሕዛብ ላይ አምጣ፡ ዘውዷ ን ያቀለለውን ደምስሰው፡ ሙፋኗን የደፈረውን ንቀለው፡ ዐሥራተ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያን ያፈረሳትን አፍርሰው። ኦ ሥሉስ ቅዱስ በደመናኤል ስምህ የቸርነትህን የይቅርታህን ደመና በኢትዮጵያ ላይ ላክ፡ በአቅናኤል ስምህ ኢትዮጵያን በአንድነት አቅናት፡ በፍታሕኤል ስምህ ኢትዮጵያን ካሰሯት አሕዛብ፡ ከስድብ ሥራ፡ ከዝሙት ሥራ፡ ከመተት ሥራ፡ ሕጻናትን ከመገበር ሥራ፡ ከአረማዊነት ሥራ፡ ከኑፋቄ ሥራ ፈጽመህ ፍታት። አቤቱ ፍቅር ከዙፋንህ የሳበህ ከሞትም ያደረሰህ የሰላም አለቃ፡ ድንቅ ጎያል አምላክ በጣኤል ስምህ ፍቅርን በኢትዮጵያ ላይ በሕዝቦቿም መካከል መሥርት።

በአማኑኤል ስምህ ኦ ክርስቶስ፡ ወልደ ማርያም፡ ወልደ አብ በኢትዮጵያ ላይ ንገሥ ክበር።

አቤቱ አምላካችን፥ እንደ ጽድቅህ ፍረድልን፥ የጋኔኑ ልጆች በላያችንም ደስ አይበላቸው።

በልባቸውም እሰይ እሰይ፥ ነፍሳችንን ደስ አላት ኢትዮጵያንም ሕፃናቷንም ዋጥ አይበሉ።

በመከራችን ደስ የሚላቸው ይፈሩ፥ በአንድነትም ይጐስቍሉ እኛን ሕዝቦችህን ግን አንድ አድርገን፤ በኢትዮጵያ ላይ የሚታበዩ እፍረትንና ጕስቍልናን ይልበሱ። የኢትዮጵያ ጽድቋን የሚወዷት ግን ደስ ይበላቸው ሐሴትንም ያድርጉ፤ የሕዝቡን ሰላም የሚወድ እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን ዘወትር ይበሉ።

ምላሴ ጽድቅህን ሁልጊዜም ምስጋናህን ይናገራል።

አቤቱ የሰራዊት ጌታ እንደ ኃጢአታችን ሳይሆን እንደ ቸርነትህ ተለመነን፡ ክፉውን ጋኔን፡ አሳቹን መንፈስ፡ እንዲሁም የዲያብሎስ እጅ የሆነውን አብይ አህመድን ከእነ ሰራዊቱ ከነጅራቱ ከኢትዮጵያ ላይ ቀስፈህ ንቀለው። ይህም ሥራ በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ስም ይደረግ። ለይኩን ለይኩን ለይኩን።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ፡ ልብሷ የወርቅ መጎናጸፊያ ነው ብሎ አስቀድሞ ዳዊት እንደተናገረ፡ የንጽሕናን የወርቅ አሸንክታብ ለአንዝረገገው ሸንጥሸ ሰላምታ ይገባል። ድንግል የዘርዓ ያዕቆብ እመቤት ሆይ ለያዕቆብ ግርማ ሞገሱ ነሽ።

የዘርዓ ያዕቆብን ምድር ኢትዮጵያን እወድሻለሁ እለን፡ የዐሥራት ሃገሬ ስትሆኝ ማነው የሚደፍርሽ የሚል ተስፋን ስጫት፡ የኢትዮጵያን ጠላቶቿን የባሮችሽንም ገዳዮች ዮሰሜር

አድሜሽ ድቸር አዶናዊሮስ ሰራስቅስርኤል በተባሉ ሃያል የጌታ ስሞች አስጥሚአቸው፡ ሰንኮፋቸውንም ከኢትዮጵያ ላይ ንቀይው፡ ለእኛ ለወገኖችሽ ሃይልን አቸናፊነትን ስጮን።"

ይህን ሰባት ግዜ የጠነከረ ግን ስድሳ አራት ግዜ ያድርሰው።

ነገሩ እንዲህ ነው፡

የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ድንግል ማርያም ደብር ምርቃት ሳይፈጸም ይህ መልእክት እንዳይወጣ ተይዞ ነበር። የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሲመሠረት የዓለም መጨረሻ እንቢልታ እንደሆነው ሁሉ፡ የዘርዓ ያዕቆብ እመቤት ቤት ምርቃትም የጋኔኑ መንፈስ በኢትዮጵያ ላይ ቅዱሳኑ ጦርነት የሚከፍቱበት፡ የኢትዮጵያም ትንሣኤ መሰረት የሚጣልበት አዋጅ ነው።

የአቡነ ሳሙኤል ልጆች መነኮሳት በየገዳማቱ አብይ አህመድን ከነሠራዊቱ እርገሙት።

የአቡነ ተክለሃይማኖት ሃዋርያት መነኮሳት የእባቡን ሎሌዎች እርገሚቸው።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ሠራዊት መነኮሳት ቀሳውስት ዲያቆናት
በቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳማትና አድባራት በድርሳነ ጊዮርጊስ ድጋም
አብይ አህመድን ከነሰራዊቱ ከነሎሌው ለሰባት ቀን እርገሙት።

"የኢትዮጵያ ኃጢአት በአቡነ ሥነ እየሱስ አምላክ ስም የተፈታ ይሁን
የኢትዮጵያ ኃጢአት በአቡነ ሥነ እየሱስ አምላክ ስም የተፈታ ይሁን
የኢትዮጵያ ኃጢአት በአቡነ ሥነ እየሱስ አምላክ ስም የተፈታ ይሁን"
ይህንን ካህናተ ኢትዮጵያ በሙሉ ያለማቋረጥ በዘመናቸው
በሙሉ ይበሉት።

የአቡነ ዘርዓ ቡሩክ ሐዋርያት መነኮሳት የኢትዮጵያ ዐይን
ይብራ፡ የጠላቷ ዐይን ይጥፋ እያላችሁ ለሰባት ቀን በጻድቁ
ስም ሱባኤ ያዙ።

አዋጅ አዋጅ
የቅዱሳን ሰራዊት በጋኔኑ መንፈስ ላይ ጦር ሰበቁ

አዋጅ አዋጅ
ኅይል አሸናፊነት ስለኢትዮጵያ ትንሣኤ ለተሰለፉ ሁሉ ታዟል

አዋጅ አዋጅ
የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር አሸናፊ ነው፡ ምርጡም
ከእንቅልፉ እንደተነሳ አንበሳ ተነስቷል።

ሕዝብ እጅህንና ልብህን ወደእግዚአብሔር ዘርጋ።
አቅመ ደካማ ጸልይ
ጎበዝ የአባቶችህን ምድር ተረከብ።

የእስማኤል ልጅ በጸሎት በቁጣ ተነሳ፡ የተጠቃው አባትህን
አክብር ጠብቅ፡ የመስቀሉም ልጆች ይህን ደግ ሰው ጠብቁት።
ሼሑ በገዳማውያን አባቶች ክብር ደርሷልና፡ መንፈሱ
ከመንፈሳቸው ይገናኛልና እሱ በሚያርፍበት ቦታ
መታሰቢያውን አቁሙለት፡ ክርስትያኑ አልቅሰው የእስማኤል
ልጆች ደረት ደቅተው በእረፍቱ ቀን ይቅበሩት። እረፍቱ
የአብርሃም ልጆች የፍቅራቸው መሠረት ይሆናል። በኢትዮጵያ
ከተነሱት ወልዮች እንደ እሱ የከበሩ ከአምስት አይበልጡምና
ክቡር ነው። የአባታችን ገብረ ሕይወት በረከት ነፍሱን
ትባርከው እሱ በተባረከው ነፍሱ ከብሮ እንጂ ቀሎ
አልተገኘምና በሕይወት እስታለ ስሙት፣ በሞቱም አክብሩት።

ተፈጠመ።